ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
MINISTRY OF INDUSTRY

# በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

# የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ ማስፈጸሚያ ማኑዋል

## (የጸደቀ)


አዘጋጆች

1. ፍቃዱ አክሊሉ
2. ፀጋዬ በንሳ
3. አማከል ሁሴን



ጥር/ 2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ ገጽ


ክፍል አንድ ፤ መግቢያ ........ 1

1.1 የመነሻ ሁኔታ ........ 1

1.2 የቃላት ፍቺና ትርጓሜ ........ 1

1.3 ወሰን ........ 3

1.4 የማንዋሉ ህጋዊ መሰረት ........ 3

1.5 ዓላማ ........ 3

1.6 ተጠቃሚዎች ........ 3

ክፍል ሁለት፡ የተግባራት ትስስር ማዕቀፍ (Framework) ........ 6

2.1 የሚከናወኑ ተግባራት አፈጻጸም ........ 7

2.1.1 እምቅ ሃብትን መለየት፣ ........ 7

2.1.2 የመሠረተ ልማት አቀርቦትን ማሻሻል ........ 8

2.1.3 የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ውህደትን ማሳደግ፣ ........ 11

2.1.4 በገጠር የአነስተኛና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋም እና ማስፋፋት ........ 14

2.1.5 የአቅም ግንባታ ስራ በዘላቂነት መስራት ........ 15

2.1.6 የፋይናንስ አቅርቦትን ማሻሻል ........ 15

2.1.7 የገበያ ተደራሽነት እና የእሴት ሰንሰለት ውህደትን ማሳደግ ........ 16

2.1.8 የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስራን በፈጠራ አዳዲስ አሰራሮችን ማፍለቅና ማዝለቅ ........ 20

2.1.9 ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት ........ 21

2.2 የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ማስተግበሪያ ስልቶች ........ 22

2.2.1 የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ........ 22

2.2.2 የማይክሮ ፋይናንስና ብድር ተቋማት እንዲቋቋም ማድረግ፡- ........ 22

2.2.3 የመንግስት-የግል ሽርክናዎች (PPPs) ማጠናከር ........ 22

2.2.4 የአቅም ግንባታ እና ስልጠና፤ ........ 22

2.2.5 የመሠረተ ልማት ግንባታ ........ 23

2.2.6 የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳለጥ ........ 23

2.3 የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስራን ለማስፈፀም የተቋማት ሚና ........ 23

2.3.1 በፌዴራል ደረጃ ያለ ሚና እና ኃላፊነት ........ 23

2.3.2 የክልል ደረጃ ያሉ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች ........ 26

2.3.3 የዞን/ወረዳ ደረጃ ያለ ሚናና ኃላፊነት ........ 27

ክፍል ሶስት፡ የማንዋሉ አተገባበር፤ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 30

3.1 ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች ........ 30

3.2 የግምገማ ና ግብረመልስ ማዕቀፍ ........ 31

3.3 ሪፖርት የማድረጊያ ጊዜ ........ 32

ዋቢ ሰነዶች ........ 32

አባሪዎች፡ ........ 33

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር ለመሳለጥ ወሳኝ ሚና ያለው ዘርፍ ሲሆን ባለፉት አመታት የውጪ ምንዛሪ ግኝት፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና ዘላቂ የሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋፅኦ እያደገ ይገኛል። ይህን ለማስቀጠልና ወደተሻለ አፈፃፀም ለማሳደግ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱ ስራዎች አንዱ በገጠሩ አካባቢ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የማቋቋምና የማስፋፋት ስራ ነው። ለዚህም በ2017 ዓ.ም የገጠር ኢንደስትሪላይዜሽን ኢኒሼቲቭ ስራ የተጀመረ ሲሆን ትግበራውን የተሳካ ለማድረግ የሚረዳና ሁሉም ተዋናዮች ወጥ የሆነ ግንዛቤና እውቀት ይዘው እንዲተገብሩ የሚያስችል የትግበራ ማስፈፀሚያ ማኑዋል ማዘጋጀት አስፈልጓል።

## 1.1 የመነሻ ሁኔታ

መንግስት ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በሰጠው ትኩረት ምቹ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መቀረፁ፣ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም እቅድ፣የሌማት ቱሩፋት፤ የ10 አመት የልማት እቅድ፣ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ፣አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ፍኖተ ካርታ፣ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ እና የተለያዩ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችና የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ተገብቷል።ይህን መነሻ በማድረግ በ2017 ዓ.ም በሀገርቱ ገጠር አከባቢዎች የሚገኙትን እምቅ ሀብቶች ላይ እሴት በመጨመር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋምና እንዲስፋፉ የገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢንሸቲቭ በማዘጋጀት ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደር ለመተግበር የሚያስችልና ወጥ የሆነ አረዳድና የትግበራ አሰራር ባለመኖሩ የአፈፃፀም ክፍተቶች ተስተውለዋል።

በመሆኑም የክልሎች/ከተማ አስተዳደር ቢሮዎች ከሚመለከታቸው የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ከሚደግፉ አመራሮች፣ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ላይ በመድረስ፤የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭን ማስፈፀሚያ ማኑዋልን ወጥ በሆነ አረዳድና የትግበራ አሰራር ወደ ስራ እንዲገቡ የሚያስችል የማስተግበሪያ ማኑዋል ማዘጋጀት አስፈልጓል።

## 1.2 የቃላት ፍቺና ትርጓሜ

**"ሚኒስቴር"** ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማለት ነው፤

**"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው

ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

**"የክልል ቢሮ"** ማለት በክልሎችና የድሬዳዋ አስተዳደር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የሚደግፍ መንግስታዊ ተቋም ማለት ነው ፣

**"ገጠር"** ማለት አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በግብርና የኢኮኖሚ መሠረት የሚተዳደርና የሚኖርበት አካባቢ፣ማዘጋጃ ቤት የሌለዉ እና ከገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢኒሼቲቭ የተለየ ባህሪ አንፃር የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሌሉባቸዉ እና ያልተስፋፉባቸዉ ወረዳዎችን/ከተሞችን የሚያካትት ነው፣

**"የገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን"** ማለት፡- በገጠር የአካባቢን ፀጋ በመጠቀም የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይራዞችን በማቋቋም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን የማስተዋወቅ፣ የማስፋፋት፤ አማራጭ የገጠር ኢኮኖሚ ለማስፋት፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ ድህነትን ለመቀነስ እና ፍትሃዊ ክልላዊ ልማትን የሚያበረታታ ነው።

**"ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዝ"** ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም የሰዉ ኃይልን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለዉጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለዉ ምርት የሚያመረት ነዉ፤

**"አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ11 እስከ 50 ቋሚ ሰራተኞች ከብር 600,001 እስከ 10,000,000 ብር (ስድስት መቶ ሺህ አንድ ብር እስከ አስር ሚሊዮን) ብር ጠቅላላ ሃብት ያለው አምራች ኢንተርፕራይዝ ነዉ፣ሆኖም ግን በሰው ሀይል እና በጠቅላላ ሀብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሀብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

**"መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ51 እስከ 100 ቋሚ ሰራተኞች ከብር 10,000,001 እስከ ብር 90,000,000 (አስር ሚሊዮን አንድ ብር እስከ ዘጠና ሚሊዮን) ብር ጠቅላላ ሃብት ያለው አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፣ሆኖም ግን በሰው ሀይል እና በጠቅላላ ሀብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሀብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

**"አዲስ የተቋቋመ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በመንግስት ድጋፍ ወይም በራሱ ጥረት በንግድ ህጉ መሰረት ህጋዊ ሰውነት ያገኘ እና በመረጠው የስራ መስክ ወደ ማምረት ተግባር የተሰማራ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ነው።

**"ነባር ኢንተርፕራይዞችን ማጠናከር"** ማለት፡- በማምረት ስራ ተሰማርቶ ሲሰራ የነበረና ስራውን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ያለበትን ክፍተት መሠረት በማድረግ በሚሰጠው ድጋፍ በምርታማነት ወይም በጠቅላላ ሃብት ዕድገት ያሳየ ወይም ተወዳዳሪ የሆነ ወይም ተጨማሪ የስራ ዕድል በመፍጠር ለውጥ ማምጣት የቻለ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ነው።

**"ቋሚ የስራ ዕድል ፈጠራ"** ማለት፡- አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ባለቤትንና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከአንድ ዓመት ላለነሰ ጊዜ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በፔይሮል ክፍያ በማግኘት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ማለት ነው::

## 1.3 ወሰን

ይህ ማንዋል በሀገሪቱ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የሚደግፉ በክልሎች/ከተማ አስተዳደር ያሉ የዘርፉ አመራሮች፣ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት እንዲሁም በገጠር በሚቋቋሙ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችና ወደ ዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ህብረት ስራ ማህበራት፣ዩኒዬኖች፣ሃብት ያፈሩ አርሶና አርብቶ አደሮች፣ የዩኒቨርሲቲ እና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን በገጠር አካባቢ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተረፕራይዞችን እዲቋቋምና እንዲሰፋፉ በማድረግ ላይ የተወሰነ ነው።

## 1.4 የማንዋሉ ህጋዊ መሰረት

የማንዋሉ ህጋዊነት በሀገሪቱ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት፣የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በሚንስትሮች ምክር ቤት ተቋማትን መልሶ ለማደራጀት በወጣው ደንብ ቁጥር 526/2015 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት፤ እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ የሀገር ውስጥ ሃብት ላይ እሴት መጨመር እና ክልሎች የተመጣጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት  እና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እድገትን ማምጣት ላይ ያተኮረና አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉ፣የስራ ፈጠራ ክህሎት እንዲያሳድግ እና በሁሉም ክልሎች ፍትሃዊ የኢንተርፕራይዞች ልማት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የተሰጠዉ ኃላፊነት እና ከሀገርቱ ሰፊ የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ልማት ዕቅዶችን መሰረት ያደረገ ሰነድ ነዉ.

## 1.5 ዓላማ

የማኑዋሉ አላማ በክልሎች/ከተማ አስተዳደር ያሉ የዘርፉ አመራሮች፣ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ዙሪያ የጋራ የሆነ ግንዛቤ በመያዝ የአከባቢዉን ዕምቅ ሀብት መሰረት በማድረግ በገጠር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ በመደገፍ የገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢኒሼቲቭን ማስፈጸም ነዉ።

## 1.6 ተጠቃሚዎች

የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ ማኑዋል ተጠቃሚዎች የዘርፉን ልማት እንዲያሳልጡ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ስለሚያስችላቸው በሀገሪቱ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የሚደግፉ ክልሎች/ ከተማ አስተዳደርና በየደረጃው ያሉ የዘርፉ አስፈፃሚዎች ባለድርሻ አካላት እንዲሁም በገጠር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በማቋቋም ወደ ዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ህብረት ስራ ማህበራት፣ዩኒየኖች፣ ሀብት ያፈሩ አርሶ

አደሮች/አርብቶ አደሮች፣የዩኒቨርሲቲ እና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን፣በሌሎች ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶች እና የገጠሩ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የተግባራት ትስስር ማዕቀፍ (Framework)

### 2.1 የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ለማስፋፋት የሚከናወኑ ተግባራት

የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ለማስፋፋት የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

### 2.1.1. እምቅ ሃብትን መለየት፣

ይህ ተግባር በክልሉ ባሉ ወረዳዎች ሁሉ ያለውን እምቅ ሃብትን በመለየት እና ለአነስተኛና መካከለኛ አምራቾች ንኡስ ዘርፎች ባለው ሃብት፣ባለው እውቀት እና በገበያ ተደራሽነት ላይ ያተኩራል::ይህም  የግብርና ምርቶች፣ ማዕድናት እና ለማኑፋክቸሪንግ ተስማሚ የሆኑ የዕደ-ጥበብ ስራዎችን የመሳሰሉ የሀገር ውስጥ ሀብቶችን መለየት፣የስልጠና ፍላጎቶችን ለመለየት የአካባቢውን ህዝብ የክህሎት አቅም መረጃ ማሰባሰብን ያካትታል።

የመሠረተ ልማት ዝርጋታ በተለይም የገጠር አምራቾችን ከትላልቅ ገበያዎች ጋር ለማገናኘት ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስን በማሻሻል፤ ኤሌክትሪክ ፣ ውሃ እና የመገናኛ አገልግሎቶች የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን እንዲደግፉ እና  ተደራሽነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ በአግባቡ መለየት፣በተለየው አቅም መሰረት በተመረጡ የማፋክቸሪንግ ዘርፎች ላይ ትኩረት በማድረግ በወረዳ ደረጃ ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል መደላድል መፍጠር።

ለዚህም ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ተስማሚ የሆኑ የግብርና ምርቶች፣ የደን፣ ለመስኖ ልማት የሚዉል የዉሃ ሀብት፣ በገጠር በቂ የሰው ሃይል መኖሩ ለዘርፉ መስፋፋት አዉንታዊ ተጽዕኖ ያላቸውን  ክልሎች/ከተማ አስተዳደር እስከ ታችኛዉ የአስተዳደር እርከን መለየትና መተንተን፤

ለገጠር ኢንስትሪላይዜሽን ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ የአከባቢዉን እምቅ ሀብት እና መሰረተ ልማት ዝርጋታን ለመለየት  ከዚህ በታች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠዉ እንደ መነሻ በመዉሰድ መስራት።

- የግብርና ሀብቶች
  - ✓ እህል:- ጤፍ፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ማሽላ ----- በብዛት የሚመረተው እና ለአግሮ ፕሮሰሲንግ (ለምሳሌ የዱቄት ፋብሪካዎች፣ የዳቦ ምርት፣ የታሸጉ እህሎች) የሚሆን፤
  - ✓ የቅባት እህሎች እና ጥራጥሬዎች:- ሰሊጥ፣ ሱፍ ፣ አኩሪ አተር፣ ሽምብራ፣ ምስር------ (ለምግብ ዘይት ምርት እና ለምግብ ማቀነባበሪያ ጥሬ ዕቃዎች የሚሆን)፣
  - ✓ የአተክልትና ፍራፍሬ ምርቶች:- ፍራፍሬዎች (ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ሲትረስ-----)፣ አትክልቶች እና ቅመማ ቅመሞች (ዝንጅብል፣ እርድ፣ ቤርበሬ-----) — (ጭማቂ መስራትን፣ አድርቆ ማሸግ እና ኤክስፖርት-ተኮር አግሪቢዝነስ የሚያገለግል) ፣
  - ✓ የእንስሳት ሀብት:- ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ የዶሮ እርባታ፣ ግመሎች - (ለስጋ ማቀነባበሪያ ፣ የወተት ተዋጽኦዎች (ወተት፣ አይብ፣ እርጎ)፣ ቆዳና ቆዳ ዉጤቶች ኢንዱስትሪዎች የሚሆን)፣
- የማዕድን ሀብቶች

- ✓ የኢንዱስትሪ ማዕድናት፡- የኖራ ድንጋይ፣ ሸክላ፣ ጂፕሰም - (በሲሚንቶ፣ በሴራሚክስ እና በግንባታ ዕቃዎች ምርት የሚያገለግል) ፣
- የደን እና የብዝሃ ህይወት ሀብቶች (Forest and Biodiversity Resources)
  - ✓ የደንና የደን ያልሆኑ ዉጤቶች፡- ቀርከሃ፣የጎማ ዛፍ፤እጣን - (በእንጨት ላይ ለተመሰረቱ ኢንዱስትሪዎች፣የጎማ ምርት፣ሙጫ ማውጣት፣ የቤት እቃዎች ማምረቻ እና የንብ ማነብ ስራ የሚሆን)፣
- የውሃ ሀብት፡- ወንዞች፣ሀይቆች የከርሰምድር ዉሃ - መስኖን ለማስፋፋት እና የዓሳ እርባታ ለማካሄድ የሚሆን
- ባዮማስ እና ባዮኤነርጂ (Biomass and Bioenergy ):- የሰብል ቅሪት፣ የእንስሳት እበት እና የእንጨት ቆሻሻ - በገጠር ኢንዱስትሪ ለኃይል አገልግሎት ሊያገለግል የሚችል፣

| ለገጠር ኢንዱስትላይዜሽን ግብዓት የሚሆኑ ሀብቶች መለያ ዘዴዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የሀብት ዓይነት | የሚሰበሰቡ መረጃዎች | የመረጃ ምንጭ | የመረጃዉ ጥቅም |
| 1 | የመሬት ሀብት | መልማት የሚችል መሬት፣ የመሬት አጠቃቀም፣የአፈር ለምነት፣ የመሬት ይዞታ ባለቤት | ግብርና መስሪያ ቤት | ለሰብል ምርት እና እንስሳት እርባታ ምቹ መሆኑን ለመለየት |
| 2 | የሰብል ምርት | በብዛት የሚመረት እህል፣ የሚመረትበት ወቅት፣ በአንድ ሄክታር የሚገኝ ምርት ብዛት፣ የመስኖ አጠቃቀም | የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ / የገበሬዎች ህብርት ስራ ማህበራት | ለአግሮ ፕሮሴሲንግ/እሴትጨምሮ ለማምረት በቂ ምረት መኖሩን ለማረጋገጥ |
| 3 | የእንስሳት ሀብት | የእንስሳት ዓይነት እና ብዛት፣ የግጦሽ ቦታ፣ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ፋሲሊቲ | የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ / የገበሬዎች ህብርት ስራ ማህበራት | ለወተት ማቀነባበር፣ ለስጋ ማቀነባበር እና ቆዳ ኢንዱስትሪ የሚሆን ፖቴንሽያል ለመለየት |
| 4 | የዉሃ ሀብት | የዉሃ ምንጭ (ወንዝ፣ሀይቅ፣ ጉድጓድ) የመስኖ ሁኔታ የዝናብ ሁኔታ) | የግብርና መስሪያ ቤት | መስኖን መሰረት ያደረገ ምርት ለማምረት እና የዓሳ እርባታ ለማካሄድ የሚረዱ ድጋፎችን ለመስጠትና/ዉሳኔ ለመስጠት |
| 5 | ስነ-ምህዳር፣ | የአየር ሁኔታ፣ የዝናብ ሁኔታ፣ የአየር ንብረት አደጋ | ግብርና መስሪያቤት/የምርምር ተቋማት/የሜትሮሎጂ ተቋም | የእህል እናእንስሳት ዓይነቶች ከአከባቢዉ አየር ጋር ቀጣይነት ያለዉ ተስማምነት ያለዉ መሆኑን ለማወቅ |

### 2.1.2. የመሠረተ ልማት አቀርቦትን ማሻሻል

የመሠረተ ልማት ዝርጋታ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እና የቅንጅት ሥራን ለማጎልበት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የውሃ አቅርቦትን የመሳሰሉ መሰረተ ልማቶችን ማሻሻል የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እና የቅንጅት ሥራን ለማጎልበት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትን ለማጎልበት፣ ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ለመቀነስ እና የገጠር ኢኮኖሚ ለውጥን ለማሳደግ መሠረተ ልማትን በገጠር አከባቢዎች ማጠናከር ወሳኝ ነው። በመሆኑም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በመለየት፤በማቀናጀትና በማስተባበር የመሠረተ ልማት ዝርጋታውን ተግባራዊ ማድረግ።

ለዚህም መረጃዎችን መሰብሰብ፣መለየትና መሟላት የሚኖርባቸዉ መሰረተ ልማቶችን እንደ መነሻ እንደሚከተለዉ ተዘርዝረዋል።

የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መረጃ መለየትን በተመለከተ

መጓጓዣ (Transportation)- ለጥሬ ዕቃዎች እና ለምርት ስርጭት (መንገዶች፣ የባቡር መንገዶች እና የትራንስፖርት አገልግሎቶች) የሚያገለግሉ፣

ኤሌክትሪክ፦ ለማሽነሪ፣ ለመብራት እና ለኦፕሬሽኖች የኃይል አቅርቦት መረጃ፣

የውሃ አቅርቦት እና የንፅህና አጠባበቅ (Water Supply and Sanitation)- የንጹህ ውሃ እና የቆሻሻ አያያዝ ስርዓቶች መኖራቸዉን፣

ግንኙነት (Communication)- የኢንተርኔት ተደራሽነት፣ ሞባይል ኔትዎርክ፣ እና የፖስታ አገልግሎቶች ፣

የፋይናንስ አገልግሎቶች - ባንኮች፣ ማይክሮ ፋይናንስ እና ዲጂታል የክፍያ ሥርዓቶች፣

የስልጠና እና የትምህርት ማዕከላት (Training and Education Centers) - የሙያ ትምህርት ቤቶች እና የክህሎት ማጎልበቻ ተቋማት፣

የገበያ መሠረተ ልማት (Market Infrastructure) - የገበያ ቦታዎች እና የንግድ ማዕከሎች

ተቋማዊ ድጋፍ (Institutional Support)- የአካባቢ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎቶች እና የንግድ ድጋፍ የሚሰጡ መስሪያቤቶች፣

በጠቅላላዉ ለገጠር ኢንዱስተሪላይዜሽን ትግበራ ሊሆኑ የሚችሉ መሰረተ ልማቶችን መረጃ እንደየ አከባቢዉ ሁኔታ በዝርዝር በመለየት፣ በማሰባሰብና በመተንተን መያዝ እና ለገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ተግባራዊነት በሚረዳ መልኩ ከሚመለከተቻዉ ባለድርሻ አከላት ጋር በመነጋገር ለታዩ ክፍተቶች መፍትሄ መስጠት፡፡

### 2.1.3. የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ውህደትን ማሳደግ፣

በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስራ ውስጥ የሚሳተፉ ቁልፍ ተዋናዮችን በመለየት እና በመተንተን የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማሳደግ፡፡ የመንግስት ተቋማት፣ የግል ባለሀብቶች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣አለም አቀፍ ድርጅቶች እና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ሚና በመለየት፤ ትብብርን ለማጎልበት እና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትን ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂ እና በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፍላጎቶች የተዘጋጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ የእያንዳንዱን ባለድርሻ አካላት ሚና፣ ፍላጎት እና ተፅእኖ በመለየት የታቀዱ የተሳትፎ ስልቶችን በማዘጋጀት ትግበራው እንዲሳለጥ ማድረግ፤ በተቀመጠው እቅድ መሰረት ስራው እየተከናወነ መሆኑን በየጊዜ እየተገመገመ እርማት እየተወሰደ የሚቀጥልበትን ስልት በመንደፍ ስራውን ተግባራዊ ማድረግ ፡፡

በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ለማሳካትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት፡፡ ለዚህም

- የዘርፉ ተጠቃሚዎችን፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚፈልጉ፤ሚና ያላቸው፤ተፅእኖ ያላቸውን በመለየት እና ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አጋር አካላትን መለየትና መተንተን፡፡
- ከባለድረሻ አካላት ጋር በተቀመጠው እቅድ መሰረት ስራው እየተከናወነ መሆኑን በየጊዜ እየተገመገመ እርማት እየተወሰደ የሚቀጥልበትን ስልት በመንደፍ ስራውን ማስቀጠል፤
- ለባለድርሻ አካላት ስለ ገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ምንነትና አስፈላጊነት ግንዛቤን የመስጨበጥ እና የማሳትፍ ስራ ማከናወን፤
- ችግር ፈቺ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር አምራቾች በሙሉ በመተማመን ኢንቨስት እንዲያደርጉ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግልጽ የሥራ ክፍፍል ማድረግ፣ ማቀድና አፈጻጸሙም ቋሚና ቀጣይነት ባለው ክትትልና ድጋፍ መምራት፤
- ከመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት (የኤሌክትሪክ ሀይል፣ መንገድ፣ ዉሃ እና ቴሌኮሙዩኒኬሽን አቅራቢዎች)፣ ከአበዳሪ ተቋማት (ልማት ባንክ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤የግል ባንኮች እና ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት)፣መሬት አቅራቢ ተቋማት፣

የግብርና ቢሮ፣ ማህበራዊ ተቋማት ዩኒቨርስቲዎች፣የምርምር ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤቶች) ስራና ክህሎት ቢሮ፣ ማዕድን ቢሮ ፣ ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ፤ የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት ትብብር ማድረግ፣ በቅንጅት መፍታት፣ የአፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ ፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በቅድመ ትግበራ ወቅት የሚፈልገውን የማምረቻ ቦታ፣ ኤሌክትሪክ፣ፋይናንስ፣ የስለጠና እና የሰው ኃይል የሚጠይቅ ነው፡፡ ወደ ምርት ከተሸጋገረ በኋላም ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል በሚፈለገው ጥራት ደረጃና መጠን ለማምረት የጥራት መሰረተ ልማቶችን ማሟላት፣ የተቀላጠፈ ሎጅስቲክስ ማቅረብ፣ ያልተቆራረጠ የግብዓት (የጥሬ እቃ)፣ የኃይልና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ማቅረብ ይጠይቃል፡፡ ባለድርሻ አካላት የየራሳቸውን ስራ ድርሻ ወስደው መስራት እና አፈጻጸሙን የሚከታተሉበት አደረጃጀት መፍጠር፡፡ ስለዚህ ዘርፉ የሚመራው ክልል/ከተማ አስተዳደር ከተመረጡ ባለድረሻ አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር የገጠር ኢንዱስትራላይዜሼንን ውጤታማ ማድረግ፡፡ ለአብነት ከሚከተሉት ባለድርሻ አካላት ጋር መስራት ይገባል፡፡

**ህብረተሰቡ/ ዜጋው፡-** የልማት አጋርነት (የባለቤትነት ስሜት፣ መነሻ ካፒታል፣ ማምረቻ ቦታ፣ አመለካከት የመለወጥ…ወዘተ) እና የሃገር ውስጥ ምርት የመጠቀም ባህልን የማዳበር ስራ መስራት፤

**በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ ህብረት ስራ ማህበራት፣ዩኒየኖች፣ ሀብት ያፈሩ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች፣ ባለሀብቶች/ና ስራ ፈጣሪዎች፡-** መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች አሟልተዉ በዘርፉ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ፤

**ለኢንተርፐራዞች ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት ፡ -** ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ተቋማት የሚገኙ የገበያ መረጃዎች በማሰባሰብና አጋርነት በመፍጠር የገበያ ትስስር መፍጠር እንዲሁም ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እርስ በእርሳቸው በምርትና ግብዓት እንዲተሳሰሩ ማድረግ፤ አምራች ኢንዱስትሪዎች በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁና እንዲሸጡ ማድረግ፣ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የራሳቸውን የንግድ ስም እና መለያ እንዲኖራቸው በማድረግ ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግ ማድረግ፡፡

**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል/አገልግሎት፡-** በገጠር ለሚቋቋሙ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፐራይዞች የመብራት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግ፣

**አነስተኛ የፋይናንስ አበዳሪ ተቋማት እና ባንኮች፡-** በስራ ማስከጃ እና በካፒታል እቃ ሊዝ ፋይናንስ አሰራር የማምረቻ መሳሪያዎችን በኪራይ ማቅረብ፣ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የስራ ማስኬጃ መስጠት፤

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት፡-** የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የሚፈልጋቸውን ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ማፍራት የሚያስችል ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ፣ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የሚፈልገውን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር፤የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣ የብቃት ምዘና ማዕከላትንና መዛኞችን በማፍራት መመዘን እና ፈቺ የሆኑ ድጋፎችን መስጠት፤

**የግብርና ተቋማት፡-** ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ግብአትነት የሚውሉ ምርቶችን በጥራት እንዲመረቱ፣ ማድረግ፤ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሆኑ ግብአቶች በወቅቱ፣ በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ማድረግ፤

**የተቀናጁ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች/ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፡-** ከፍተኛ አምራች ኢንተርፕራይዞችን ከአነስተኛና መካከለኛ አምራት ኢንዱስሪዎች ጋር በግብዓት፣ በምርት፣ በቴክኖሎጂና የሰው ሃይል አቅርቦት ትስስር መፍጠር፤

**የማሽነሪዎች አምራቾች ማህበር፡-** የማሽነሪ አምራቾች ማህበራት በገጠር ላሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማሽነሪዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

**ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች፡-** የህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች አርሶ አደሮችን/አርብቶ አደሮችን በማሰባሰብ የጋራ ተግባርና የሀብት ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪነግ ኢንዱስትሪዎችን እንዲያቋቁሙ ማድረግ፤

**መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡-** ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት፣ አነስተኛ ፋይናንስ እና የኢንቨስትመንት እድሎችን በማመቻቸት፤ የንግድ እድገትን፣ ፈጠራን በመደገፍ ምርታማነትን እና ተወዳዳሪነትን ከሚያሻሽሉ ጋር ተቀናጅቶ መስራት፤

### 2.1.5 በገጠር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋም እና ማጎልበት

በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የገጠር ወረዳዎች በተለየው እምቅ ሀብትና በተጠናው የንዑስ ዘርፍ ልየታ መሰረት ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ለማቋቋም የሚችሉ ዜጎችን መለየት፣ የመስሪያ ቦታ፤የፋይናንስ፤የገበያ፤የክህሎት፤እና የመሳሰሉትን ድጋፎች እንዲመቻቹ በማድረግ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖች፤ ሀብት ያፈሩ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች፣ የዩኒቨርሲቲና ቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች እና በሌሎች ዘርፎች

ላይ ተሰማርተዉ የሚገኙ ባለሀብቶች  በዘርፉ ላይ ግንዛቤ እንዲገኙ በማድረግ ወደ ዘርፉ እስኪገቡ ድጋፍ በማድረግ፡፡

እንደ ማሳያ  በገጠር ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚሰማሩበት ንኡስ ዘርፎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- **ጨርቃጨርቅና አልባሳት ማምረቻ  ንኡስ ዘርፍ**

***ሀ/ ጨርቃጨርቅ ማምረት*** (Textile)፡-

- ጭረቶችን(ክሮችን) ማዘጋጀት፣መፍተል፣መሸመን፣ማጠናቀቅ
- የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆችን ወይም ሹራብ ወይም ምንጣፍ ማምረት፤

***ለ/ አልባሳት ማምረት*** (Garment)

- የጨርቃጨርቅ አልባሳትን ማምረት፣ የሹራብ ሥራ፣ፎጣ ማምረት፣ የጥልፍ ሥራ ብርድልብስ ፣ የተዘጋጁ የማስዋቢያና  የጨርቃጨርቅ ቁሳቁሶች ማምረት

- **ምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ንኡስ ዘርፍ**

***ሀ/የምግብ ኢንዱስትሪ***

- ሥጋና የሥጋ ዉጤቶች ማቀነባበር፣ ዓሳና የዓሳ ዉጤቶችን ማቀነባበር፣ አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበር
- የምግብ ዘይት ማምረት
- ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ዉጤቶችን ማምረት
- የእህል ምርት ዉጤቶችን ማቀነባበር (ዱቄት ማምረትን ሳይጨምር)
- ማካሮኒ፣ ፓስታ እና /ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት
- አዮድን የተጨመረበት ጨዉ ማምረት
- ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት
- የእንስሳት መኖ ማቀነባበር፣ የኦቾሎኒ ቅቤ ማምረት፣ማር እና ሰም ማቀነባበር፣ ጥራጥሬ የቅባት እህል ማቀነባበር
- የቅመማ ቅመም ማቀነባበሪያ፣ ዱቄት ማምረት

***ለ/ የመጠጥ ኢንዱስትሪ***

- የአልኮል መጠጥ ማምረት፣የወይን ጠጅ ማምረት
- የማዕድን ወይም የታሸጉ ለሎች ዉሃዎችን ማምረት፣

- **ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ**

- የቆዳ ዉጤቶች እና/ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት
- የቆዳ ጫማ ማምረት
- የቆዳ ልብሶች ፣ የጉዞ ዕቃዎች ፣ የሴቶች የእጅ ቦርሳ ፣ ቦርሳዎች ፣ ኮርቻ እና ልጉዋም ማምረት

- **ኬሚካል ዉጤቶች ኢንዱስትሪ**

- የንፅህናና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች (ሳሙና፣ የውበት እቃዎች፣ ለሽቶ የሚያገለግሉ ኬሚካሎች የመዓዛማ ዘይቶች ማምረት)

- **የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ውጤቶች**

- የማዋቀሪያ እና የተለያዩ የብረታ ብረት ዉጤቶችን ማምረት
- በርና መስኮት ሥራዎች ፣ቀላል ማሽነሪዎችን ማምረት
- ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ማምረት፣የማሽነሪ መለዋወጫዎች

- **የእንጨትና ቀርከሃ ዉጤቶች ኢንዱስትሪ**

- የእንጨት ዉጤቶችን ማምረት
- የቀርከሃ ዉጤቶችን ማምረት
- እንጨት መሰንጠቅና ማለስለስ በአግባቡ መያዝና ማምረት
- የእንጨት ተረፈ ምረቶች ቡሽ ፣ ገለባ እና የመሳሰሉት ማምረት
- ሌሎች እንጨት መሰንጠቅና ማለስለስ የእንጨት ተረፈ ምርቶች ማምረት

- **የዕደ ጥበብ ዉጤቶችና ጌጣጌጥ ማምረቻ**

- የከበሩ ድንጋዮች ማስጌጥ ሥራ፣የነሐስ ጌጣጌጥ ሥራ፣የአሸንጉሊት ስራ፣ የሙካሽ ሥራ

- **የግንባታ ግብዓት ምርቶችን ማምረት**

- ብሎኬት፣ቴራዞ ማምረት፣ ኮንክሪት ፖል ማምረት፤ባዞላ ማምረት፤ ጅብሰም የመሳሰሉትን ማምረት፣

- **ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ**

- የሸክላ ዉጤቶች ማምረት

- የድንጋይ ዉጤቶችን፣ ዕብነ በረድ እና ግራናይት የኖራ ድንጋይ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርጽ ማውጣት እና ማጠናቀቅ
- ኖራ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን ማምረት

**አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ለማቋቋም የሚከናወኑ ተግባራት**

- በእምቅ ሀብትና የንዑስ ዘርፍ ልየታ መሰረት በአካባቢው ለመገኙ ወደ ስራው ለሚገቡ ዜጎች ግንዛቤ መፍጠር፤
- የአዋጭነት ጥናት/ቢዝነስ ፕላን ማዘጋጀት፤
- የማምረቻ ቦታ/ሼድ በራስ /በመንግስት ማዘጋጀት፤
- አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ ፈቃዶችን እና የአካባቢ ጥበቃ ደንቦችን፣የጤና እና የደህንነት ደረጃዎችን ፈቃዶችን ጨምሮ ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ፣
- የፋይናስ አቅርቦት (ስራ ማስኬጃ እና ካፒታል ሊዝ) ሊገኙ የሚችልባቸውን አማራጮች መፍጠር (ለምሳሌ አነስተኛ የብድር አቅራብ ተቋማት፣ የማሽን ሊዝ ተቋማት፣ የህብረት ስራ ማህበራት፣ባንኮችና የመሳሰሉት)
- መሰረተ ልማት (መብራት፤ ዉሃ፤ መንገድ፤) በተመሟላባቸው አካባቢዎች ስራ በማስጀመር ባልተሟላባቸው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መስራት፤
- የሥራ ፈጠራ እና በተመረጠው የስራ መስክ ክህሎት ቴክኒካል ስልጠና መስጠት፤
- የማሽን ተከላ ፣ለናሙና ምርት የተግባር ሥልጠና መስጠትና የሙከራ ምርት ማምረት (commissioning) ስራዎች ላይ ድጋፍ መስጠት፤
- ገበያ፣የግብይት እና የማስተዋወቅ ስትራቴጂዎች በመንደፍ ጠንካራ ማንነትን(branding) ለመፍጠር እንዲችሉ ማድረግ፤
- የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤

### 2.1.6. የአቅም ግንባታ ስራ በዘላቂነት መስራት

- አቅምን ማሳደግ ማለት ግለሰቦች፣ ተቋማት ወይም ማህበረሰቦች የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሰልጠን እና ግንዛቤ በመፍጠር በብቃት ማከናወን ያለባቸውን ክህሎቶች፣ ዕውቀት፣ ስልቶች እና ግብአቶች የማጎልበት እና የማጠናከር ሂደት ነው።
- በኢትዮጵያ ካለው የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት አንፃር የገጠር ነዋሪዎችን ከኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል አቅምን በማሳደግ ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ መስራት፤

➢ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የንድፈ ሀሳብ እና ተግባር ተኮር ስልጠና መስጠት ፡፡ በተለይ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ዜጎች ወደ ስራ በሚገቡበት መስክ ፣የአጫጭር የስራ አመራር እና ክህሎት ስልጠና በየደረጃው ከሚገኙ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለስራ ብቁ ሊያደርጋቸው የሚችሉ አጫጭር የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና መስጠት፤

በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን የአቅም ግንባታ ስራ ዘርፈ ብዙ አካሄድን ያካተተ ሲሆን በዋናነት የንድፈ ሀሳብ እና ተግባር ተኮር ስልጠና ላይ ያተኩራል፡፡ በባለድርሻ አካላት፣ ስራ ፈጣሪዎች እና ሰራተኞች መካከል የግንኙነት (communicati0n) ፣ የቡድን ስራ እና ችግር የመፍታት ችሎታን ስለሚያሳድግ፣ ጠንካራ ትብብር እና ቀልጣፋ የስራ አካባቢን ለማጎልበት የንድፈ ሀሳብ ስልጠና አስፈላጊ ነው፡፡

የገጠር አምራቾችን የበለጠ ለማጎልበት በአቅም ግንባታ እና በቴክኒክ ድጋፍ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ በአመራረት፣በማቀነባበር፣በግብይት እና በጥራት ቁጥጥር ላይ ባሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ የስልጠና መርሃ ግብሮችን መስጠት በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላትን ክህሎት እና እውቀት ማሳዳግ ተገቢ ነው፡፡በተጨማሪም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና ልምዶችን ለመቅሰም ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት ምርታማነትን ያሳድጋል፣ የምርት ጥራትን ያሻሽላል እና በመጨረሻም የገበያ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ በመሆኑ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት የሚከናወኑ ተግባራት**

- የክህሎት ክፍተቶችን በጥናት መለየት፤
- የስልጠና ፍላጎት መጠይቅ ማዘጋጀት (በስልጠና ፍላጎት መለያ ቅጽ መሰረት)፤
- ስልጠናውን ሊሰጡ የሚችሉ ተቋማትን  መለየት፤
- የስልጠና ማኑዋል /ሰነድ ማዘጋጀት፤
- የስልጠና ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትና ማጸደቅ፤
- የንድፈሃሳብና የተግባር ስልጠና ለተጠቃሚው መስጠት፣
- የስልጠና እርካታ መጠይቅ ማስሞላት (በስልጠና መለኪያ ቅጽ መሰረት)፤
- የስልጠና እርካታ መለካት፤

- የአቅም ግንባታ ስልጠና የወሰዱት ላይ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ፤
- በስልጠና የመጣ ዉጤትን ፋይዳዊ ግምገማ ጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፤
- በግምገማው መሰረት ለውጥ ያላመጡትን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ለቀጣይ ስልጠና ግብዓት መለየት፤

### 2.1.7. የፋይናንስ አቅርቦትን ማሻሻል

ሃገራችን ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገትና የገጠር ልማትን ለማስፋፋት ጥረት ቢታደርግም በገጠራቱ ኢትዮጵያ የፋይናንስ አቅርቦት አሁንም ትልቅ ፈተና ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው በገጠር ሲሆን ግብርና የመተዳደሪያ ምንጭ ነዉ። ነገር ግን በገጠር ያለው የፋይናንስ አገልግሎት ውስን የሆነው የመሰረተ ልማት አለመዘርጋት፣ የፋይናንስ እውቀት ዝቅተኛነት እና መደበኛ የባንክ ተቋማት ባለመኖራቸው ነው።

የገጠር ነዋሮዎች እና ኢንተርፕራይዞች ብዙ ጊዜ መደበኛ ባልሆኑ የብድር ሥርዓቶች ላይ ጥገኛ ናቸው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግስት የገጠርን የፋይናንስ አቅርቦት ለማሻሻል እንደ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ የህብረት ስራ ባንክ እና የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎቶችን አስተዋውቋል።

በገጠር ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦትን ለማሻሻል ሁለገብ አቀራረብ አስፈላጊ ነው። ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ ልማት ባንክ፣ የንግድ ባንክ እና የግል ባንኮች ተደራሽነትና አሰራር (ተስማሚ የወለድ መጠኖችን እና የብድር አማራጮችን) ማመቻቸት። የብድር ስጋቶችን ለመቀነስ ግልጽ ፖሊሲዎችን እና የብድር ዋስትና መርሃ-ግብሮችን ማቋቋምና ማጠናከር።

ለዚህም የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል

- **የፋይናንስ እውቀት እና አቅም ግንባታ፡-** በፋይናንስ አስተዳደር፣ በሒሳብ አያያዝ እና በንግድ እቅድ ላይ የሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ ስለ የፋይናንስ አቅርቦት አይነቶች እና አገልግሎቶች ግንዛቤን ማሳደግ፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የአበዳሪ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የንግድ ፕሮፖዛል እና የብድር ማመልከቻዎችን በማዘጋጀት መደገፍ፤
- **ብድር ማመቻቸት፡-** አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ ከባንኮች እና ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር ማገናኘት፤ የመንደር ቁጠባና ብድር ማኅበራትን መመስረትን መደገፍ፤
- **የዲጂታል እና የሞባይል ፋይናንሺያል አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ፡-** ለብድር አከፋፈል፣ ቁጠባ እና ክፍያዎች የሞባይል ባንኪንግ ማስተዋወቅ፣ ርቀው በሚገኙ

አካባቢዎች ዝቅተኛ ወጪ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ተቋማት ጋር መተባበር፤

## 2.1.8. የገበያ ተደራሽነት እና የእሴት ሰንሰለት ውህደትን ማሳደግ

### 2.1.8.1. የገበያ መዳረሻ

- በገጠር ማኑፋክቸቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች፣ ግብዓት አቅራቢዎች፣ ገዢዎች እና ሸማቾች መካከል ያለውን ግንኙነት በማመቻቸት የዚህን ውህደት ጥቅም ከፍ ለማድረግ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ማስቻል፤
- በገጠር አካባቢ የሚመረቱ ምርቶች ወደ ገበያዎች እንዲደርሱ አሰራሮችን መዘርጋት፣ የገጠር ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዞች ከከተሞች እና ከአለም አቀፍ ገበያ ጋር እንዲወዳደሩ ማድረግ፤
- የገጠር ኢንዱስትሪዎች የምርት ሂደታቸውን እንዲያሳድጉ እና በገበያ የሚፈለጉትን የጥራት ደረጃዎች የሚያሟሉ ምርቶችን እንዲያመርቱ ማድርግ፤

የገበያ ተደራሽነትን ለማሳደግ ስልታዊ አካሄድን መዘርጋት ያስፈልጋል። ለዚህም የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አስፈላጊ ነዉ፡-

- የገበያ ተደራሽነትን በማሻሻል አምራቾች ሽያጫቸውን ማሳደግ፣ ተፈላጊነታቸውን ሊያሳድጉ እና ለአካባቢው ኢኮኖሚ ልማት አስተዋፅዖ እንዲያድርጉ ማስቻል፣
- የሀገር ውስጥ የንግድ ማህበራትን ማለትም የንግድ ምክር ቤቶችን መቀላቀል እና ከመንግስት አካላት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ግብአትና ስልጠና ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ፣
- የአካባቢ እና የክልል የገበያ ፍላጎቶችን ለመረዳት፣ ደንበኞችን እና ተወዳዳሪዎችን ለመለየት እንዲሁም የምርት ፍላጎትን እና የሸማቾችን ምርጫዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ አዝማሚያዎችን ለመተንተን የገበያ ጥናት ማካሄድ፣
- ምርቶችን በማህበራዊ ሚዲያዎች፣ በማህበረሰብ ዝግጅቶች ፣ሚዲያ እና መድረኮች በማስተዋወቅ ከአካባቢው ሸማቾች ጋር የሚስማማ ጠንካራ የምርት መለያ እንዲመሰርቱ ማድረግ፣
- ከአቅራቢዎች እና ከአፋፋዮች ጋር ግንኙነቶችን በመገንባት የጥሬ እቃና ምርቶች አስተማማኝ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ የማከፋፈያ ቻናሎችን እንዲያሳድጉ ማስቻል፣
- የአሰራር ቅልጥፍናን ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ማጎልበቻ ፕሮግራሞችን እንዲያገኙ ማድረግ፣

- የገበያ ተደራሽነት ስትራቴጂዎችን በመደበኛነት በመገምገም አፈፃፀሙን መከታተል እና መገምገም እና የግብረመልስ ዘዴዎችን በመዘርጋት ቀጣይነት ወዳለው መሻሻል የደንበኞችን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፣

በአጠቃላይ ይህንን የተቀናጀ አሰራርን በመከተል የገበያ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማሻሻል እና በማህበረሰቡ ውስጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንዲያበረክቱ እና በመጨረሻም የገጠር አካባቢዎችን አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንዲያሻሽሉ መስራት።

### 2.1.8.2. የእሴት ሰንሰለት ልማት እና ውህደት

የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ የእሴት ሰንሰለት ልማትና ውህደት እያንዳንዱን የምርት ደረጃ ከጥሬ ዕቃ ማምረቻ እስከ የመጨረሻ ምርት ስርጭት በማስተሳሰር የገጠር ኢንዱስትሪዎችን ቅልጥፍናና ተወዳዳሪነት ማሻሻል ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት።

እነዚህን በተሳለጠ መልኩ ለማከናወን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል።

- በአርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች እና በማኑፋክቸሪንግ ኢንተረፕራይዞች መካከል ያለውን የገበያ ግንኙነት ማጠናከር። ለአብነት መሠረተ ልማትን ማሳደግ፣ የአምራቾችን አቅም ማሳደግ፣ የጥራት ደረጃዎችን ማሳደግ እና የተሻለ የገበያ ትስስር መፍጠር
- የእሴት ሰንሰለቱን በማቀናጀት የገጠር ኢንዱስትሪዎች ምርታማነትን ማሳደግ፣ ወጪን መቀነስ እና በገበያ ተወዳደሪ በመሆን በገጠር ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት፣
- የጥሬ እቃ፣ ምርት፣ ግብይት እና ስርጭት ያሉ ዋና ዋና ተግባራትን በመለየት የእሴት ሰንሰለቱ ሂደቱን ማወቅ፣
- ከአቅራቢዎች፣ አምራቾች፣ አከፋፋዮች እና ደንበኞችን ጨምሮ መሻሻል ያለባቸውን ቦታዎች በመለየት ግንኙነት ማጠናከር፣
- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀበል እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የምርት ሂደቶችን በማሳደግ የበለጠ ውጤታማነትን እና የምርት ጥራት መሻሻል ላይ መስራት፣
- ለኢንተርፕራዞች የአመራረት፣ የጥራት ቁጥጥር እና ሎጅስቲክስ አስተዳደር ክህሎትን እንዲያሳድጉ ማድረግ፣

- የእሴት ሰንሰለት ቁልፍ የስራ አፈጻጸም አመልካቾችን (KPIs) በማስቀመጥ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፣
- በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብርን ማሻሻል እና የፈጠራ ባህልን ማሳደግ፣ አዳዲስ ምርቶችን ለገበያ ማቅረብ እና ያሉትን ሂደቶች ማሻሻል፣

### 2.1.9. የገጠር ኢንዱስተሪያላይዜሽን ስራን በፈጠራ አዳዲስ አሰራሮችን ማፍለቅና ማዝለቅ

በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ካለው የገጠር ኢንዱስተሪያላይዜሽን ልማት አንፃር ዘላቂነት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን::

- የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች የአካባቢን ስነ-ምህዳሮች ወይም የተፈጥሮ ሃብቶችን እንዳይጎዱ ማረጋገጥ እና በየደረጃው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ መስራት፣
- በገጠር ኢንዱስተሪያላይዜሽን እንቅስቃሴ ማህበራዊ እኩልነት እና ፍትሃዊ አሰራሮችን ማሳደግ እና ለአካባቢው ማህበረሰቦች የአኗኗር ዘይቤ እንዲሻሻል ማድረግ፣
- ስራ መፍጠር እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማጎልበት የአካባቢ እና ማህበራዊ ደረጃዎችን እንዲሻሻል ማድረግ፣

**ፈጠራ (INNOVATION)**

ፈጠራ ቀጣይነት ያለው አሰራርን ለመምራት እና በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ምርታማነትን ለማሳደግ ወሳኝ ነው:: በመሆኑም የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አስፈላጊ ነዉ::

- ውጤታማነትን የሚያሻሽሉ፣ ብክነትን የሚቀንሱ እና ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የሚያበረታቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- የአገር ውስጥ ሥራ ፈጣሪዎችን የሚያበረታቱ እና የገበያ መዳረሻን የሚያመቻቹ አዳዲስ የንግድ ሞዴሎችን ማዘጋጀት፣
- በመንግስታት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግሉ ሴክተር ሀብቶችን እና እውቀትን ለመጋራት አጋርነትን ማበረታታት፣

### 2.1.10. ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት

ተሞክሮን መቀመርና ማስፋት ዓላማው በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ትግበራ የተሳካላቸዉ ሞዴል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዞችን ወይም የአሰራር ምርጥ ተሞክሮ ወደ ሌሎች ክልሎች/ዞኖችነ ወረዳዎች በተጣጣመ ሁኔታ

ማስፋፋት ሲሆን በርካታ የማስፋፊያ መንገዶችን መከተል ያስፈልጋል። ይህም ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸዉ፣ በመንግስታዊ እና የግል ሚዲያ እና በተለያዩ የማህበራዊ የመገናኛ ዜዴዎች እና በመድረኮች ከገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢንሽቲቭ ጋር በማጣጣም ወጥነት ባለዉ ሁኔታ መስራት ያስፈልጋል።

- ምርጥ ተሞክሮ ማለት ለአንድ ድርጅት አፈጻጸም መሻሻል አስተዋፅኦ ያበረከቱ ብልጫ ያለውን ዘዴና ፈጠራ የተሞላበት ተግባር የሚያሳይ እና ይህም በአብዛኛው ተመሳሳይ ድርጅቶች እውቅና የተቸረው ብልጫ ያለው ልምድ ነው።

**የምርጥ ተሞክሮ ዓይነቶች**

| ተ.ቁ | የምርጥ ተሞክሮ ዓይነቶች | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1 | በተግባር የተፈተሹ ምርጥ ተሞክሮዎች /Field tested best practice/ | በሥራ ላይ ውለው ስኬታማ ውጤት ያስገኙ ፕሮግራሞች፣ ተግባሮች ወይም ስትራቴጂዎች ናቸው። |
| 2 | በትግበራ ላይ ያሉና ተስፋ ሰጪ ምርጥ ተሞክሮዎች /Promising best practice/ | በአንድ ተቋም/ሴክተር ውስጥ በሥራ ላይ የዋሉ ፕሮግራሞች፣ ተግባሮች ወይም ስትራቴጂዎች ሲሆኑ በመጀመሪያ የሙከራ ጊዜ ላይ ተስፋ ሰጪ ውጤት እየሰጡ ያሉ |
| 3 | በምርምር የተረጋገጡ ምርጥ ተሞክሮዎች /Research Validated best practice/ | ውጤታማነታቸው በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ እና ሁሉንም ባካተተ መልኩ በምርምር የተረጋገጡ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ዋና ዋና ተግባራቶችና ስትራቴጂዎች ናቸው። |


**ዋና ዋና የምርጥ ተሞክሮ መገለጫ ባህሪያት፡-**

- የለውጡ አድማስ ሠፊ መሆኑ
- ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው
- በቀላሉ የመስፋፋት ዕድል ያለውና ልዩነት የሚፈጥር መሆኑ
- ፈጠራ የታከለበት አሰራር ያለው
- በአቅማችን ልንተገብረው (Affordable) ደጋግመን ለመጠቀም ተጨማሪ ወጪ የማያስወጣን ሊሆን የሚገባው መሆኑ
- ከጊዜ አኳያ ፈጣን ስርነቀል ለውጥ የሚያመጣ (Swift and revolutionize in terms of speed)

- ተፅእኖው ወይም የግብ ስኬቱ ሊቀለበስ የማይችል እና ለረዥም ጊዜያት የሚቆይ መሆኑ (Irreversible and sustainable in terms of impact)

**የምርጥ ተሞክሮ አዘገጃጀት ሂደት**


- ምርጥ ተሞክሮ ዝግጅትና ትግበራ ሶስት ዋና ይዘቶች ያሉት ሲሆን አንዱ ከአንዱ ጋር ያለው የመመጋገብ ሁኔታ እጅግ የተሳሰረ ነው፡፡




**የምርጥ ተሞክሮ ዑደት**

በጠቅላለዉ ተሞክሮ መለየት መቀመርና ማስፋት ዓላማው በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ትግበራ የተሳካላቸዉ ሞዴል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዞችን ወይም የአሰራር ምርጥ ተሞክሮ ወደ ሌሎች ኢንተርፕራይዞች/ ክልሎች በተጣጣመ ሁኔታ ማስፋፋት ሲሆን በርካታ የማስፋፊያ መንገዶችን መከተል ያስፈልጋል፡፡ ይህም ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸዉ፣ በመንግስታዊ እና የግል ሚዲያ፣ በተለያዩ የማህበራዊ የመገናኛ ዜዴዎች እና በመድረኮች ከገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢንሼቲቭ ጋር በማጣጣም ወጥነት ባለዉ ሁኔታ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**የተግባራት ትስስር ማሳያ**



እምቅ ሃብትን መለየት
የመሠረተ ልማት አቀርቦትን ማሻሻል
የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ውህደትንማሳደግ፣
በገጠር የአነስተኛና አነስተኛኢንተርፕራይዞች ማቋቋም እናማስፋፋት-
የአቅም ግንባታ ስራ በዘላቂነት መስራት
የፋይናንስ አቅርቦትን ማሻሻል
የገበያ ተደራሽነት እና የእሴት ውህደትን ማሳደግ
የገጠር ኢንዱስተሪያላይዜሽን ስራን በፈጠራ አዳዲስ አሰራሮችን ማፍለቅና ማዝለቅ
ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት

## 2.2. የገጠር ኢንዱስተሪያላይዜሽን ማስተግበሪያ ስልቶች

### 2.2.1. የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ

- እሴት በመጨመር ለግብርና ምርቶች (ለምሳሌ ቡና፣ እህል፣ ፍራፍሬ) ዋጋን እና የገበያ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የማቀነባበሪያ ፋሲሊቲዎችን ማቋቋም፣
- የህብረት ስራ ማህበራት፣አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች እና የግል ባለሀብቶች በማቀናጀት የማቀነባበሪያ ፋሲሊቲዎች ላይ በጋራ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

### 2.2.2. የማይክሮ ፋይናንስና ብድር ተቋማት እንዲስፋፉ ትኩረት ማድረግ፡-

- የካፒታል አቅርቦትን ለማቀላጠፍ ለገጠር ሥራ ፈጣሪዎች የብድርና የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት የማይክሮ ፋይናንስና የብድር ተቋማትን ማቋቋም፣ማስፋፋት፤
- ለገጠር ኢንደስትሪ ፕሮጀክቶች የተለየ የኢንቨስትመንት ፈንድ መፍጠር የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን በማሳደግ እና የስራ እድሎችን መፍጠር ላይ ትኩረት ማድረግ፣

### 2.2.3. የመንግስት-የግል ሽርክናዎች (PPPs) ማጠናከር

- በመንግስትና በግሉ ሴክተር መካከል ያለውን ትብብር ማበረታታት ግብአትን፣ እውቀትንና ቴክኖሎጂን ለገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ማዋል፣
- በመንግስት፣ በግሉ ሴክተር እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መካከል ያለውን ትብብር ሀብትን እና እውቀትን ለመጠቀም ማበረታታት፣

### 2.2.4. የአቅም ግንባታ እና ስልጠና፤

- የገጠር የሰው ሃይል ክህሎትን ለማሳደግ የስልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና በመተግበር የአዲስና ነባር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ፍላጎት ማሟላት፣
- በገጠር ፈጠራን እና የንግድ ስራን በሚያበረታቱ የትምህርት ተነሳሽነት ስራ ፈጠራን ማሳደግ፣

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ የንቅናቄ መድረኮችን መፍጠር፣

### 2.2.5. የመሠረተ ልማት ግንባታ

- የሸቀጦች እና አገልግሎቶችን እንቅስቃሴ ለማመቻቸት መንገዶችን እና የትራንስፖርት ስርዓቶችን ማሻሻል፣
- የኤሌትሪክ እና የታዳሽ የኃይል ምንጮችን ተደራሽነት ወደ ገጠር ማስፋፋት፣
- በገጠር ውስጥ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ እንደ ውሃ፣ ኢንተርኔት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘትን ተደራሽ ማድረግ፣

### 2.2.6. የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳለጥ

- ምርታማነትን ለማሳደግ ዘመናዊ የግብርና እና የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን ማሳደግ፣
- ከዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር ለገጠር አካባቢዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር እና ማላመድ፣

## 2.3. የገጠር ኢንዱስተሪያላይዜሽን ስራን ለማስፈፀም የተቋማት ሚና

በፌዴራል ደረጃ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መሪነት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢንሼቲቭ ስራን የሚያስተባብር ሲሆን በክልል በዞንና በወረዳ ደረጃ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን በሚደግፉ ተቋማት አስተባባሪነት የሚመራ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል፣በክልል፣በዞንና በወረዳ የኢንሼቲቭ ስራውን የሚያስተባብሩ ባለሙያዎች (focal person) ተወክለዋል፡፡

### 2.3.1. በፌዴራል ደረጃ ያለ ሚና እና ኃላፊነት

#### 2.3.1.1.የፖሊሲ፣ የድጋፍ ማዕቀፍ እና የማበረታቻዎች መቅረፅ

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ለማነቃቃት የሚያስችሉ የፖሊሲ ድጋፍ እና አስቻይ ሁኔታ መፍጠር፤
- የአነስተኛና መካካለኛ አምራቾች እድገትን የሚያበረታቱ ሀገራዊ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት እና መደገፍ፤ በተለይም በገጠር አካባቢ ያሉ አምራች ኢንተርፕራይዞችን የሚደግፍ የህግ ማዕቀፍ መቅረፅን ያካትታል።
- አሰራሮችን በማቀላጠፍ እና ማበረታቻዎችን በማቅረብ፣ መንግስት ለአነስተኛ እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን እድገት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤

#### 2.3.1.2. የመሠረተ ልማት ግንባታ

- የገጠር አነስተኛና መካካለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞችን እድገት ለማፋጠን ጠንካራ መሠረተ ልማት ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ይህ በተለይ የሚዘጋጁ የኢንዱስትሪ ክላስተር እና ሼዶች እንዲመሰርቱ መደገፍ፣አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን መሙዋላታቸውን መከታተላል ፤ መደገፍ፤ ከመንግስት እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የመንገድ፣ የሃይል፣ የውሃ እና የኮሙኒካሽን መሠረተ ልማቶችን ለማሻሻል ከባለድርሻዎች ጋር መስራት፤

#### 2.3.1.3.. የፋይናስ ድጋፍን ማመቻቸት

- የፋይናንስ አቅርቦት ለገጠር አነስተኛና አነስተኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች እድገት ወሳኝ ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በተለይ ለገጠር ኢንዱስትሪዎች **የፋይናስ** ድጋፍ ፕሮግራሞችን ፣ የብድር ዋስትናዎችን እና የገንዘብ ድጎማዎች ከባለድርሻዎች ጋር እንዲዘጋጁ ማመቻቸት፤
- ከባንክ እና ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የተጣጣሙ የፋይናንስ አቅርቦትን እንዲፍጠር ማመቻቸት፤
- በገጠር ያሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለማሳደግ እና ለማጠናከር የሚያስፈልጋቸውን የፋይናንስ ምንጭ ከባለድርሻዎች ጋር እንዲያገኙ ማስቻልን።

#### 2.3.1.4.. የምርምር እና ልማት ስራ

- በገጠር ያሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እያጋጠሟቸው ባሉ ተግዳሮቶች እና እድሎች ላይ ምርምር ማድረግ በሚገኝ የጥናት ውጤት መሰረት የፖሊሲ ውሳኔዎችን እና የድጋፍ ፕሮግራሞችን በማወቅ ጠቃሚ የፖሊሲ ሃሳብ እንዲቀርብ ማድረግ፤
- የምርምር ተቋማትን እና ዩኒቨርሲቲዎችን በማቀናጀት ፈጠራን በማበረታታት እና ትብብርን በማጎልበት አዳዲስ ምርቶችን እና የተሻሻሉ የምርት ሂደቶችን እንዲያመጡ ማድረግ፤

- የእውቀት ሽግግር መድረኮችን ለመፍጠር ከዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር የገጠር ስራ ፈጣሪዎችን አዳዲስ መረጃዎችን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ያሉን ሀብቶችን ፣ ክህሎቶችን እና እምቅ አቅም ያላቸው ዘርፎችን ለመለየት ሀገራዊ ጥናቶችን ማካሄድ ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ቦታዎችን እና የድጋፍ አይነቶችን በመለየት መምራት፤

### 2.3.1.5. የአቅም ግንባታ እና የስልጠና ፕሮግራሞች

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስራን ለማጎልበት በአቅም ግንባታ እና በስልጠና ፕሮግራሞች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ወይም ድጋፍ የሚሰጡ አካላትን በማፈላለግ አነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በገጠር ኢኮኖሚው ላይ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ለማጉላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማድረግ፤
- በአውደ ጥናቶች፣ ሴሚናሮች እና ዲጂታል መድረኮች ባሉ ሀብቶች፣ የድጋፍ መርሃ ግብሮች እና ምርጥ ተሞክሮዎች መረጃን መስጠት ስኬታማ ለመሆን በሚያስፈልጋቸው እውቀት ማስታጠቅ ፤
- ከገጠር ኢንዱስትሪዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ክህሎት ለማዳበር ሀገራዊ የሥልጠና መርሃ ግብሮችን መተግበር እና ከትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ፍላጎቶች ላይ ያተኮረ የሙያ ስልጠና መፍጠር የሰለጠነ የሰው ኃይል ማብቃት፤
- ለክልል እና ለዞን/ወረዳ አስፈፃሚ ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ሀገር አቀፍ የስልጠና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት
- በፌዴራል ደረጃ ላሉ ባለድርሻ ተቋማት ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚያደርጉት ድጋፍ ያላቸውን አቅም ማጎልበት የሚያስችል ስልጠና መስጠት
- ከዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር የእውቀት ሽግግር መድረኮችን መፍጠር በገጠር አነስተኛ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መካከል ፈጠራን እና ስራ ፈጣሪነትን ማጎልበት።እና በፌዴራል ደረጃ የሚሰሩ የገጠር ኢንደስትሪያላይዛሽን ስራዎችን ይሰራል።

### 2.3.1.6. የገበያ መዳረሻ እና የእሴት ሰንሰለትን ማስተዋወቅ

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ስኬት ለማረጋገጥ የገበያ ተደራሽነትን ማመቻቸት እና ምርቶቻቸውን ማስተዋወቅ ማለትም አነስተኛ የንግድ ትርዒቶችን እና የኤግዚቢሽኖችን ተሳትፎን ማመቻቸትን ጨምሮ ለምርቶቻቸው ገበያዎችን በመለየት እና በማግኘት ላይ እገዛ ማድረግ፤
- የሀገር ውስጥ ምርቶችን በገጠር ምርቶች ፍላጎት፣ ዋጋ አወጣጥ እና አዝማሚያ ላይ መረጃን በማቅረብ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የንግድ ሥራ ውሳኔ እንዲያደርጉ ማድረግ፤

- በገጠር አምራቾች እና በትላልቅ ገዥዎች መካከል ያለውን ሽርክና ማመቻቸት የእሴት ሰንሰለቶችን በማጠናከር አጠቃላይ የገበያ ሁኔታን እንዲሻሻል ማድረግ፡፡

## 2.3.2. የክልል ደረጃ ያሉ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች

### 2.3.2.1. የክልል እቅድ እና ስትራቴጂ ልማት

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን በብቃት ለማራመድ ከፌዴራል ፖሊሲዎች ጋር የሚጣጣሙ ክልላዊ ኢንደስትሪላይዜሽን ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት፤
- በክልል ሃብት ላይ ተመስርቶ የማደግ አቅም ያላቸውን የተወሰኑ ዘርፎችን በመለየት ጥረታቸውን በማነጣጠር የእነዚህን ዘርፎች ልማት መደገፍ፤
- የክልሉን ባለድርሻ አካላት፣ የማህበረሰብ መሪዎችን፣ አርሶ አደሮችን እና የንግድ ባለቤቶችን ዩኒየንና ኮፕሬቲቭስ በእቅድና ትግበራ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ ተሳትፏቸውን እና እገዛቸውን ማረጋገጥ፤
- የክልል አማካሪ ምክር ቤቶችን መፍጠር የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የበለጠ ለማጠናከር እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ቀጣይነት ያለው ተሳትፎን ማረጋገጥ፤

### 2.3.2.2. ሀብት መመደብ እና የፋይናስ ድጋፍ

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ጅምር ስኬትን ለማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ለመደገፍ የክልል በጀት እና ግብዓቶችን መመደብ ወሳኝ ነው፡፡
- የማይክሮ ፋይናንስ እና የብድር አገልግሎት እንዲቋቋም ማመቻቸት፤
- የክልል መንግስታት የፋይናስ ተቋማትን በማስተባበር የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስራን በልዩ ሁኔታ የሚደግፉበትን መንገድ ማመቻቸት የኖርበታል፡፡

### 2.3.2.3. የገበያ መዳረሻ እና ትስስር

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስኬትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የገበያ ተደራሽነትን እና ትስስርን ማመቻቸት፤
- በገጠር አምራቾች እና በከተማ ገበያዎች መካከል ያለውን ትብብር ማመቻቸት፣ የንግድ ትርዒቶችን እና ኤግዚቢሽኖችን በማዘጋጀት የገጠር ምርቶችን ለማስተዋወቅ እና የገጠር ምርቶችን ፍላጎት፣ ዋጋ እና አዝማሚያ መረጃ ማቅረብና የክልል የገበያ መረጃ ስርዓት መፍጠር፤
- በገጠር አምራቾች እና በትላልቅ ገዥዎች መካከል ያለውን ሽርክና ማመቻቸት የእሴት ሰንሰለቶችን ማጠናከር እና አጠቃላይ የገበያ ሁኔታን ማሻሻል፤

### 2.3.2.4. የሀብት መለያ እና የማስተዋወቅ ስራ

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን በብቃት ለመደገፍ በክልሉ ያለውን የተፈጥሮና የሰው ሃይል በመለየት ግምገማ ማካሄድ፤

- የክልሉን የሀብት መሰረት በመረዳት ለኢንዱስትሪ ስራዎች የሀገር ውስጥ ሃብትን በዘላቂነት እንዲጠቀሙ ማበረታታት፤
- ክልሉን በገጠር ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ማራኪ መዳረሻ አድርጎ በንቃት ማስተዋወቅ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣት ካፒታል እና እውቀትን መሳብ፤

#### 2.3.2.5. የመሠረተ ልማት ግንባታ

- ለገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ወሳኝ የሆኑ መሠረተ ልማቶች እንዲመሟሉ ማድረግ፤
- የአካባቢ መሠረተ ልማት ከታዳጊ የገጠር ኢንዱስትሪዎች ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ከወረዳ አስተዳደር ጋር መስራት፤
- ወሳኝ በሆኑ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ እንደ መንገድ፣ ኤሌክትሪክ እና ቴሌኮሙኒኬሽን ኢንዲሟሉ ማድረግ፤

#### 2.3.2.6. የአቅም ግንባታ እና የቴክኒክ ድጋፍ

- የንቅናቄ መድረኮችን በመፍጠር በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ መስራት፤
- የአካባቢ ማህበረሰቦችን እና አምራቾችን ለማጎልበት በአቅም ግንባታ እና በቴክኒክ ድጋፍ ስራ ላይ ትኩረት ማድረግ፤
- ከገጠር ኢንዱስትሪዎች ጋር ተያያዥነት ባላቸው እውቀትና ልምዶች ላይ ያተኮሩ የሥልጠና እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ከሚመለከታቸው ተቋማት በትብብር መስራት፤
- በክልሉ ውስጥ ላሉ የገጠር ኢንዱስትሪዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ በንግድ ልማት፣ ግብይት እና ቴክኖሎጂ እውቀት ማግኘትን ጨምሮ ስራቸውን እና ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያደርጉበትን ስልጠናዎች መስጠት፤
- የእውቀት ሽግግር መድረኮችን በማመቻቸት ከዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር ፈጠራን እና ስራ ፈጣሪነትን ማዳበር፤
- በክልሉ ውስጥ ላሉ የገጠር ኢንዱስትሪዎች ፤ባለድርሻ አካላትና አስፈፃሚ አካላት እና የማህበረሰብ መሪዎችን የሚያሳትፉበት የክልል አውደ ጥናቶችን እና ሴሚናሮችን በማካሄድ የክልል ኢንዱስትሪያላይዜሽን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመለየት የትብብር ስራን ማመቻቸት፤

### 2.3.3. የዞን/ወረዳ ደረጃ ያለ ሚናና ኃላፊነት

#### 2.3.3.1. ሀብት መመደብ እና የፋይናስ ድጋፍ እንዲያኙማድረግ

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ጅምር ስኬትን ለማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጡ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን ለመደገፍ የክልል በጀት እና ግብዓቶችን መመደብ ወሳኝ ነው፡፡

- በገጠር አካባቢው የሚገኙ የፋይናስ ተቋማትን በማስተባበር፣በተለይ አነስተኛ የማይክሮ ፋይናንስ እና የብድር አገልግሎት ሰጪዎች አዲስ ለሚቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች የፋይናስ ችግር መፍቻ አድረጎ በመውሰድ አበክሮ መስራት፤

#### 2.3.3.2. የክህሎት ልማት እና ስልጠና

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስኬት ለማረጋገጥ በክህሎት ልማትና ስልጠና ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤
- ለአካባቢው ነዋሪዎች እና አዲስ ወደ ስራው ለሚገቡ ዜጎች የስልጠና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፤
- ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከሀገር ውስጥ የትምህርት ተቋማት ጋር መተባበር የስልጠና ፕሮግራሞችን ተደራሽነት እንዲሰፋ ማድረግ፤
- የሥልጠና መርሃ ግብሮች ትኩረት መሆን ያለበት በአካባቢው የሚፈጠሩትን ኢንዱስትሪዎች ፍላጎት የሚያሟላ የሰለጠነ የሰው ኃይል መገንባት ላይ ነው።
- በወረዳው አንደኛ ደረጃ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከሚያስፈልጉት ልዩ ሙያዎች ጋር የተጣጣሙ የአካባቢ የሥልጠና መርሃ ግብሮችን መተግበር ስልጠናው ተገቢ እና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፤

#### 2.3.3.3. በገጠር የመሠረተ ልማት መሻሻል

- ለገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የአካባቢ መሠረተ ልማትን ማሻሻል አስፈላጊ ነው። ይህንን የኢንዱስትሪ ስራዎችን ለመደገፍ እንደ የመስሪያ ቦታ ኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦትን እና የመገናኛ ዘዴዎች የመሳሰሉ የአካባቢ አገልግሎቶችን ማሳደግ፤
- የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ከሰፊ የኢንደስትሪ ልማት ግቦች ጋር እንዲጣጣሙ እና አስፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍና ድጋፍ እንዲያገኙ ከዞንና ከክልል መንግስታት ጋር የተቀናጀ አካሄድን መከተል፤
- የገጠር ኢንዱስትሪዎችን የሚደግፉ አነስተኛ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለመለየት እና ለመተግበር ከማህበረሰቡ አባላት ጋር መስራት ማህበረሰብን ማሳተፍ እና የአካባቢ ልማት ተነሳሽነቶችን ባለቤትነት እንዲኖር መስራት፤

#### 2.3.3.4. የአካባቢ ሥራ ፈጣሪነትና የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት

- አዳዲስ የአነስተኛ እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙና ነባሮቹ እንዲጠናከሩ አጠቃላይ የድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት፤
- የአንድ መስኮት አገልግሎት ማዕከላትን በመቋቋምና በማጠናከር የምክር አገልግሎት የንግድ ልማት ስልጠና፣በገበያ ዕድሎች ላይ መረጃ መስጠት፤ የህግ ምክር እና የቴክኒክ ድጋፍን የሚያካትቱ ፓኬጆችን ማቅረብ፤

- የአገር ውስጥ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በገጠር ኢንዱስት ስራ ውስጥ ያላቸውን ሚና በመለየት ተሰትፎቸውን ማሳደግ፤
- የኢኮኖሚ እድገትን እና የስራ እድልን ለመፍጠር ለሀገር ውስጥ ስራ ፈጣሪዎችና ለአነስተኛና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጠንካራ ድጋፍ መስጠት ወሳኝ ነው። ይህ የፋይናንስ አስተዳደርን፣ ግብይትን እና ኦፕሬሽንን ጨምሮ የተለያዩ የንግድ ሥራ አመራርን የሚሸፍኑ አጠቃላይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን መስጠትን ያካትታል።

# ክፍል ሶስት

# የማንዋሉ አተገባበር፤ ክትትልና ግምገማ ስርዓት

የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ክትትልና ግምገማ የኢንዱስትሪ ልማት የገጠር ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅዖ እና ለአካባቢ ጥበቃ ዘላቂ እንዲሆን ወሳኝ ሚና አለው። በሚገባ የተቀናጀ  የክትትል እና የግምገማ ማዕቀፍ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ ማስተካከያዎችን ለማድረግ ይጠቅማል፣ አጠቃላይ የገጠር ኢንዱስትሪያዊ ውጥኖችን ስኬት ያሳድጋል። የዚህ የክትትል እቅድ ዋና አላማ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፕሮግራም ሂደትን መከታተል፣ የታቀዱትን አላማ ማሳካታቸውን ማረጋገጥ እና ውሳኔ ሰጪዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማስተካከያ እንዲያደርጉ እውነተኛ መረጃን ማቅረብ ነው።

## 3.1. ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች

የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፕሮግራም አፈጻጸምን ለመከታተል እና ለመገምገም የሚለካ ቁልፍ የሥራ አፈጻጸም አመልካቾችን (KPIs) ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። እነዚህ አመልካቾችን(KPI) በገጠር የተቋቋሙ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር፣ የተፈጠረ የስራ እድል ፈጠራ፣ የሀገር ውስጥ ምርትና ምርት ዕሴት ጭማሬ እና የፋይናንስ አቅርቦት መሻሻል ሊያካትቱ ይችላሉ። እነዚህን አመላካቾች በመከታተል ፖሊሲ አውጪዎች እና ባለሙያዎች የጣልቃ ገብነትን ተፅእኖ በመገምገም ስልቱን ለማመቻቸት በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ማድረግ ያስችላሉ።

የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ አፈጻጸምን ለመከታተል እና ለመገምገም የሚያስችል ቁልፍ የሥራ አፈጻጸም አመልካቾችን (KPIs) የሚከተሉትን ይመስላል፤

የሥራ አፈጻጸም አመልካቾችን (KPIs)

| **ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች**(KPI) | የሥራ አፈጻጸም አመልካቾችን (KPIs) |
|---|---|
| የተቋቋሙ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች | በንዑስ ዘርፍ የተቋቋሙ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች ብዛት |
| እሴት መጨመር | ወደ የተጠናቀቁ ምርቶች የተሰሩ ጥሬ እቃዎች መጠን |
| የተፈጠረ የስራ እድል | በገጠር ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የተፈጠሩ ሥራዎች ብዛት / ሴቶች እና ወጣቶች መቶኛ |
| የአቅም /ችሎታ እድገት | ስልጠና የወሰዱ ሠራተኞች ብዛት<br>ስልጠና የተሰጠበት የሙያ እና የሙያ ፕሮግራሞች ብዛት |
| የፋይናንስ መዳረሻ | ለገጠር ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የብድር/የክሬዲት/የማሽን ኪራይ ውል መጠን እና የፋይናስ ተጠቃሚ የሆኑ ንተርፐራይዞች ብዛት |
| የገበያ መዳረሻ | የተፈጠረ የገበያ ትስስር ብዛት/ተጠቃሚ የሆኑ ንተርፐራይዞች ብዛት |
| የኢኮኖሚ እድገት | የጠቅላላ ክልላዊ ምርት (ጂአርፒ) ጭማሪ<br>ከገጠር ኢንዱስትሪዎች ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ዋጋ |

## 3.2. የግምገማ ና ግብረመልስ ማዕቀፍ

- የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ ስራን የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ በየደረጃው ከሚገኙ የክልል አስፈጻሚ፣ ፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት ጋር በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት፣ በዘጠኝ ወራት እና በዓመት የሚደረግ ሲሆን ግምገማውም ፕሮግራሙን ማጠናከር የሚያስችል ይሆናል፤
- በኢኒሼቲቩ እቅድ አፈጻጸም ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶችና ግምገማዎች የሚደረስባቸው ድምዳሜዎች በአግባቡ እየተያዙ ግምገማውን መሰረት ያደረገ ግብረ መልስ ለሚመለከታቸው አካላት በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት፣ በዘጠኝ ወራት እና በዓመት በጽሑፍ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

3.2.1. የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን

- ምልከታ (Observation) በማድረግ፣/የመስክ ግምገማ፤
- ከክልሎች ፣ከከተማ አስተዳደር፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር መረጃ ልውውጥ በማድረግ፤
- የስልክ ንግግሮችን በማድረግ፤
- በበይነ መረብ በሚደረጉ ውይይቶች፤
- አጫጭር ስብሰባዎችን በማካሄድ፤
- የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገም፤

### 3.3. ሪፖርት የማድረጊያ ጊዜ

ከበጀት ዓመቱ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ ዕቅድ አኳያ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የግምገማ ሪፖርት ሲዘጋጅ የዕቅዱ ቁልፍ አፈፃፀም የውጤት አመልካቾች (Output Indicators) ታሳቢ ባደረገ አግባብ የሚፈፀም ሆኖ የሪፖርት አቀራረብ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| የሚሰበሰቡ መረጃዎችና ሪፖርት የሚሸፍኑት ጊዜ | ሪፖርት አቅራቢዎች | ሪፖርቱ የሚቀርብለት አካል |
|---|---|---|
| አመታዊ (ከሰኔ 22-26) | ክልሎች | የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበላይ አመራሮች እና በማናጀንመንት እንዲገመገም ከተደረገ በኋላ ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር ይቀርባል፡፡ |
| ስድስት ወራት (ከታህሳስ 22-26) | ክልሎች | የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበላይ አመራሮች እና በማናጀንመንት እንዲገመገም በኋላ ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር ይቀርባል፡፡ |
| በየሩብ ዓመት (ከመስከረም፣ከመጋቢት 22-26) | ክልሎች | የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበላይ አመራሮች እና በማናጀንመንት እንዲገመገም በኋላ ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር ይቀርባል፡፡ |
| ወርሃዊ (በየወሩ ከ 22-26 ) | ክልሎች | የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼቲቭ አስተባባሪዎች |

## ዋቢ ሰነዶች


- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊስ ታህሳስ 2016 ዓ.ም አዲስ አባባ ኢትዮጵያ
- ደንብ ቁጥር 526/2015 የኢትዮድያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ፤
- Project Proposal on 3-2-1 Rural Industrialization Initiative in Ethiopia Prepared by: Ministry of Industry (ከመንደር ወደ ሃገር በኢንዱስትሪ መሻገር) November 2024, Addis Ababa
- Ethiopia Manufacturing SME Development Roadmap, 2023 G.C.
- Investment Potentials in Ethiopia Envestment Commission, 2022 G.C.
- የኢትዮድያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስትራቴጂክ ዕቅድ 2012 — 2022 E.C.
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ ሰኔ 2014 አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፖሊሲ ህዳር፣ 2016 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

# አባሪ

**የመሰረተ ልማት መረጃ ልየታ ቅጽ**

| ተ.ቁ | የመሰረተ ልማት ዓይነት | መሰረተ ልማቱ አሁን ያለበት ሁኔታ | የተለየ የመሰረተ ልማት ክፍተት | የመሰረተ ልማቱ ሁኔታ በገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ላይ ያለዉ ተጽዕኖ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |